Leiden
The Netherlands

Leiden - The Hague
The Netherlands

Royal Netherlands Embassy
Addis Ababa, Ethiopia

*Translated (Amharic) StRA Briefing Paper no. 5*

# የፖሊሲ አጭር መግለጫ

# በአማራ ብሔራዊ ክልል የሴቶችን ውሳኔ ሰጪነት ብቃት በተመለከተ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት

በተስፋነሽ ታደሰ (ፒ ኤች ዲ)[1]

መስከረም 2015 (E.C.)

**Publisher's Note:** ASCL, UL and the NL Embassy stay neutral with regard to jurisdictional claims in this series regarding any published maps, institutional affiliations, and related material.

**Copyright:** © 2023 by the author. Submitted for possible open access publication under the terms and conditions of the Creative Commons Attribution (CC BY) license (https://creativecommons.org/licenses/by/4.0/).

[1] Gondar University (College of Social Science and Humanities), Gondar, Ethiopia. E-mail: tesfagondar@yahoo.com.

**አጭር ማጠቃለያ**: ይህ ጥናት በአማራ ብሄራዊ ክልል በቤተሰብ ደረጃ የሴቶችን ውሳኔ ሰጪነት ብቃት በተመለከተ የተከናወነ የዳሰሳ ጥናት ነው። ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ለጥናቱ አላማ ሲባል በተዘጋጀ የተደራጀ የዳሰሳ ጥናት መጠይቅ ቅጽ በመጠቀም ከ ታህሳስ 2013- የካቲት 2014 ዓ.ም ድረስ ከ424 በትዳር ላይ ካሉ ሴቶች ላይ የተሰበሰበ ነው። የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ለመለካት የተለያዩ ጠቋሚዎችን በመጠቀም ውሳኔ ሰጪነት እና የሃብት ባለቤትነት የሚሉ ሁለት መመዘኛዎች ተጠቅመናል። ይህ ጥናት 91 ከመቶ የሚሆኑት የጥናቱ ተሳተፊዎች የውሳኔ ሰጪነት ብቃት እንዳላቸው ያሳያል። የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው አጠቃላይ የሴቶች ውሳኔ ሰጪነት ብቃት ከፍተኛ መሆኑን ነው። በተጨማሪም ሴቶች ከጤና ጋር በተያያዘ ያላቸው ውሳኔ ሰጪነት እና የሃብት ባለቤትነት ላይ ከፍ ያለ ተሳትፎ እንዳላቸው ያሳያል። በሌላ በኩል ጥናቱ የተካሄደበት ዞን፣ የመኖሪያ አካባቢ ከተማ ወይም ገጠር መሆን፣ የባል የትምህርት ደረጃ እና በማህበረሰብ ስብስቦች ላይ ተሳትፎ ማድረግ የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ደረጃ የሚወስኑ ሁኔታዎች እንደሆኑ ጥናቱ ያመለክታል። በመጨረሻም የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ለማሻሻል እና ያለበትን ደረጃ ለማስጠበቅ በፖሊሲ የተደገፈ የሴቶችንና የወንዶችን የትምህርት ደረጃ ማሻሻል፣ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ማድረግ እንዲሁም የሴቶችን ተሳትፎ የሚያሳንሱ ልማዳዊ አስተሳሰቦችንና እምነቶችን መለወጥ ያስፈልጋል።

**ቁልፍ ቃላት**: ሴቶች፤ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ብቃት፤ በቤተሰብ ደረጃ ውሳኔ ሰጪነት፤ በቤተሰብ ደረጃ የሃብት አሰተዳደር፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል፤ ኢትዮጵያ

## 1. መግቢያ

በማደግ ላይ በሚገኙ ሃገራት የሚኖሩ ሴቶች አፍሪካን ጨምሮ በአጠቃላይ ህብረተሰባዊ ተሳትፎአቸው አናሳ ከመሆኑ በተጨማሪ በኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ችግሮች ምክንያት ድምጻቸው የታፈነ ነው[1] ። ምንም እንኳ ሴቶች 50 ከመቶ የሚሆነውን የማህበረሰብ ክፍል የሚወክሉ ቢሆንም በተለያዩ ማህበራዊ እና ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ከወንዶች እኩል የመሳተፍ መብት ተነፍገዋል። በአሁኑ ወቅት የሴቶች መብቃት የአለምአቀፍ የልማት ፖሊሲ እና ትግበራ ዋና የውይይት ማእከል ሆኗል። ሴቶች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የሚያደርጉት ተሳትፎ ለአንድ ማህበረሰብ አጠቃላይ ልማት አስፈላጊ ነው። ይህንንም ለማረጋገጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል እድል ሊሰጣቸው ይገባል። በሌሎች ታዳጊ ሀገራት እንደሚኖሩ ሴቶች ሁሉ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሴቶችም ማህበራዊ ሚናቸውን እና ሰብዓዊ ክብራቸውን ዝቅ የሚያደርጉ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ፈተናዎች ያጋጥሟቸዋል[2] ። ይህን እውነታ በመገንዘብ የኢትዮጵያ መንግስት የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ወስዷል። ከተወሰዱ የህግ ማሻሻያ ማዕቀፎች መካከል የ1987 ህገ-መንግስት፣ የ1993 የቤተሰብ ህግ፣ የሚሊኒየም የልማት ግቦች ይገኙበታል። ይሁን እንጂ እሰካሁን ድረስ በኢትዮጵያ የሴቶች እኩል ተሳትፎ አልተረጋገጠም። የሴቶች ውሳኔ ሰጪነት በኢትዮጵያ የአማራ ክልልን ጨምሮ ዝቅተኛ ነው። ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ድሃ ናቸው፣ የትምህርት ደረጃቸው ዝቅ ያለ ነው፣ በተለይ በገጠራማ አካባቢዎች በግብርና ስራ በጉልበታቸው ለሚያበረክቱት አሰተዋጽዖ ተገቢውን እውቅና አያገኙም። በመጨረሻም ሴቶች ዋና ውሳኔ ሰጪነት ስልጣን የላቸውም[3] ። አሁናዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የክልል ምክርቤት ሴቶች 94 መቀመጫዎችን በመያዝ 37 በመቶ ብቻ ድርሻ አላቸው። በሌላ በኩል ሴቶች በክልል ደረጃ ያሉ የቢሮ ሃላፊነት እና ምክትል ሃላፊነት ደረጃ 17 በመቶ፣ በዞን ደረጃ 22 በመቶ እና በወረዳ ደረጃ 23 በመቶ በሴቶች የተያዙ ሃላፊነቶች ናቸው[4] ። ከዚህ መረጃ የምንረዳው

ነገር የሃላፊነት ደረጃዎች ከፍ እያሉ በሄዱ ቁጥር በሴት ሃላፊዎች የመያዛቸው እድል እየቀነሰ እንደሚሄድ ነው፡፡ ስለሆነም እስካሁን ድረስ በፖለቲካና በሃላፊነት ዙሪያ የሴቶች ተሳትፎ የፍትሃዊነት ችግር እንዳለበት ያሳያል፡፡ በዚህ ጥናት የሴቶች ውሳኔ ሰጪነት ብቃት የሚለውን ቃል ብያኔ የሰጠን ሲሆን በዚህ ጥናት የሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ማለት በሁሉም የህይወታቸው ጉዳይ አቅማቸውን ተጠቅመው የራሳቸውን ውሳኔ መስጠት መቻል፣ በሃብታቸው እና በህይወት ምርጫዎቻቸው ላይ የማዘዝ ስልጣን መኖር ማለት ነው፡፡ ያሉትን ክፍተቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ሴቶች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ ጉዳዮች የላቀ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ የሴቶችን ውሳኔ ሰጪነት ማሳደግ ብዙ ውስብስብ ሂደት የሚፈልግ እና ብዛት ያላቸውን ተግባራት የሚጠይቅ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም በአማራ ብሄራዊ ክልል የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ደረጃ ለመዳሰስ ነው፡፡

## 2. የጥናቱ ስልት

ይህ ጥናት የተካሄደው በአማራ ብሄራዊ ክልል ነው፡፡ የ2006 የማዕከላዊ ስታትስቲክስ  ኤጀንሲ መረጃን በመጠቀም በተተነበየው መስረት የ2010 የክልሉ አጠቃላይ የህዝብ ብዛት 21136526 (ወንድ፡-10586829 እና ሴት፡-10549697) ነው[5] ፡፡ ጥናታችን መረጃዎችን በአሃዛዊ መንገድ የመተንተን ዘዴን የተከተለ ሲሆን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንም በዋናነት በትዳር ላይ ያሉ ሴቶችን በመጠየቅ የተገኘ ነው፡፡ በሌላ በኩል ተጨማሪ መረጃዎች ከታተሙ ጽሁፎች፣ ከአለማቀፋዊ ተቋማት ሪፖርቶች እና የጥናት ጽሁፎችን ወስደናል፡፡ በጥናቱ 424 ያገቡ ሴቶች የተሳተፉ ሲሆን የጥናቱ ተሳተፊዎችን ለመለየት ለሁሉም ተሳታፊዎች እኩል የመሳተፍ እድል የሚሰጠውን ባለብዙ ደረጃ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ተከትለናል፡፡ በከተማ እና በገጠር ያለውን የሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ልዩነት ለማየት እንዲቻል የጥናቱ ተሳታፊዎች ከከተማ እና ከገጠር ቀበሌዎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ መረጃውን ለመሰብሰብ የቤተሰብ የዳሰሳ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ለመወሰን በቤት ውስጥ ያላቸውን የውሳኔ ሰጪነት እና የሃብት ባለቤትነትን እንደ ዋና መለኪያ ተጠቅመናል፡፡ እነኝህ ሁለቱ መለኪያዎች እያንዳንዳቸው ሰፋ ያሉ ዝርዝር ጠቋሚዎች አሏቸው፡፡ የጥናቱን ውጤት ገላጭ በሆኑ መለኪያዎች ለማቅረብ ተችሏል፡፡

## 3. የጥናቱ ውጤት

### በቤተሰብ ደረጃ የተደረገ የሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ብቃት የዳሰሳ ጥናት ውጤት

በአጠቃላይ 289 (68 ከመቶ) የሚሆኑት የጥናቱ ተሳታፊ ሴቶች ብቻቸውን ወይም ከትዳር አጋራቸው ጋር በመሆን በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ የጤና ጉዳዮችን በተመለከተ 383 (90 ከመቶ)፤ የግል ጉዳዮችን በተመለከተ 272(64 ከመቶ) የሚሆኑት ሴቶች ውሳኔ ላይ ይሳተፋሉ፡፡ በአጠቃላይ 343 (81 ከመቶ) የሚሆኑ የጥናቱ ተሳታፊ ሴቶች በሃብቶቻቸው ላይ ውሳኔ በመስጠት ይሳተፋሉ፡፡ ይህ ውጤት እንደሚያመለክተው አብዛኛው ሴቶች 386 (91 ከመቶ) የውሳኔ ሰጭነት ብቃት አላቸው፡ ይህም ውጤቱ አዎንታዊ እንደሆነ ያሳያል፡፡ የሴቶችን ጥቅል የውሳኔ ሰጪነት ብቃት በአራቱ መመዘኛዎች የሚያሳይ ሰንጠረዥ ከዚህ በታች ቀርቧል (ሰንጠረዥ 1)፡፡

**ሰንጠረዥ 1፡ የውሳኔ ሰጪነት ብቃት በአራቱም መለኪያዎች በመቶኛ**

| **መለኪያ** | **ቁጥር** | **በመቶኛ** |
|---|---|---|
| ኢኮኖሚያዊ ውሳኔ ሰጪነት | 289 | 68 |
| ጤናን በተመለከተ ውሳኔ ሰጪነት | 383 | 90 |
| በግላዊ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሰጪነት | 272 | 64 |
| የሃብት ባለቤትነት | 343 | 81 |
| **ጥቅል የውሳኔ ሰጪነት ብቃት** | **386** | **91** |

ምንጭ፡- የዳሰሳ ጥናት ውጤት፣ 2014

**ውሳኔ ሰጪነት**

ጥቅል የሆነው የኢኮኖሚያዊ ውሳኔ ሰጭነት ውጤት ከፍ ያለ ቢመስልም 330 (78 ከመቶ) የሚሆኑት የጥናቱ ተሳታፊ ሴቶች የእራሳቸው የሆነ የባንክ ሂሳብ የላቸውም። ይህም ማለት ጥናቱ በተካሄደበት ቦታ የሚኖሩ ሴቶች ኢኮኖሚያዊ ችግር እንዳለባቸው ያመላክታል። በተጨማሪም 57 ከመቶ የሚሆኑት ሴቶች በምንም አይነት የገቢ ማመንጫ ስራ ላይ አልተሰማሩም። የገቢ ማመንጫ ስራ ላይ ያለ ተሳትፎን በተመለከተ 76 ከመቶ በገጠር ቀበሌዎች የሚኖሩ ሴቶች የገቢ ማመንጫ ስራ ላይ የማይሳተፉ ሲሆን 39 ከመቶ የሚሆኑት በከተማ ቀበሌዎች የሚኖሩ ሴቶች በምንም አይነት የገቢ ማመንጫ ስራ ላይ ተሳትፎ አያደርጉም ። ይህም በገጠር አካባቢ ያለውን የሴቶች የኢኮኖሚ ጥገኝነት በግልጽ የሚያሳይና የኢኮኖሚያዊ ውሳኔ ሰጪነታቸውን በቀጥታ የሚጎዳ ነው። በዚህ ጥናት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው 146 (34 ከመቶ) ሴቶች እራሳቸው በሚያገኙት ገንዘብ ተጠቅመው በእራሳቸው ውሳኔ የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ለምሳሌ ልብስና ጌጣጌጥ መግዛት አይችሉም ወይም እንዲገዙ አይፈቀድላቸውም። ይህ ሁኔታ ከማህበረሰባዊ እና ባህላዊ ተጽዕኖዎች ጋር የተያያዘ እና በአብዛኛው ወንዶች የቤተሰብ ሃላፊ በሆኑበት ሁኔታ ሴቶች በዋና ዋና ወጪዎች ላይ ውስን ተሳትፎ እንደሚያደርጉ አመላካች ነው። ይህ ሁኔታ በተለይ ደግሞ በገጠራማ አካባቢዎች በጣም የከፋ ነው። አንዲት የጥናቱ ተሳታፊ ከምዕራብ ጎጃም እንደገለጹት፡

"…….ባለቤቴ የቤተሰቡ አስተዳዳሪ/ቀላቢ ስለሆነ በማንኛውም ውሳኔ ላይ እኔ አልሳተፍም፤ በተለይ ደግሞ በቤት ውስጥ ባሉ ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎች ላይ ተሳትፎ የለኝም"።

ይህ ውጤት በግልጽ እንደሚያመለክተው በገንዘብ ጉዳይ የሴቶች ተሳትፎ በጣም አናሳ መሆኑን ነው። ምንም እንኳ ጥቅል የሴቶች ውሳኔ ሰጪነት ብቃት ከፍ ያለ ቢሆንም በአንዳንድ የተለዩ የኢኮኖሚዊ ጉዳዮች ላይ በተለይም በገጠር አካባቢዎች ብዙ መሰራት እንዳለበት ነው።

የምግብ ግብዓቶችን ግዥ እና ለምግብ የሚወጣ ገንዘብ መጠንን በተመለከተ ብዙዎቹ 265 (63 ከመቶ) በጋራ እንደሚወስኑ የገለጹ ሲሆን ባሎች(ወንዶች) ብቻ 99 (23 ከመቶ) እንዲሁም ሚስቶች (ሴቶች) ብቻ 59 (14 ከመቶ) ውሳኔ እንደሚሰጡ ገልጸዋል። ይህ ሁኔታ ከአሁን በፊት ከወጣው የጥናት ውጤት[6] የተለየ ነው። ይህ ጥናት እንዳመለከተው የምግብ ወጪዎችን በተመለከተ ከፍተኛውን የውሳኔ ድርሻ የሚይዙት ሴቶች ናቸው።

በቤት ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ሃብቶችን ለምሳሌ ከብቶች፣ በጎች፣ ፍየሎች፣ ቴሌቪዥን፣ ሶፋ፣ አልጋ፣ ማቀዝቀዣ (ፍሪጅ) የመሳሰሉትን ለመግዛት፣ ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ ቢፈለግ 291 (69 ከመቶ) የሚሆኑት በጋራ የሚወስኑ ሲሆን 109 (26 ከመቶ) ባሎች(ወንዶች) ብቻ እና 24 (5 ከመቶ) ሚስቶች (ሴቶች) ብቻ እንደሚወስኑ ገልጸዋል። ይህ ሁኔታ ሴቶች ከፍ ያለ ዋጋ በሚያወጡ ሃብቶች ላይ ዝቅተኛ የውሳኔ ሰጪነት ተሳትፎ እንዳላቸው ያሳያል።

**የሃብት ባለቤትነት**

በዚህ ጥናት ብዙዎቹ  ዋና ዋና የሚባሉ ንብረቶችን ማለትም መሬት፣ ቤት እና ከብቶች የመሳሰሉ ንብረቶቻቸውን ባል እና ሚስት በጋራ በባለቤትነት እንደሚያስተዳድሩ ያሳያል። ይሁን እንጂ መሬትን በተመለከተ 55 (15 ከመቶ) ባሎች ብቻቸውን ባለቤት እንደሆኑ ሲገለጽ በአንጻሩ 24 (7 ከመቶ) ደግሞ ሴቶች በብቸኝነት የመሬት ባለቤት መሆናቸውን ገልጸዋል። ሌሎች ሃብቶችን ለምሳሌ ቤት እና ከብቶች ላይ ደግሞ 324 (76 ከመቶ) በጋራ ባለቤት የሆኑ ሲሆን ባሎች(ወንዶች) ብቻ 38 (9 ከመቶ) እና ሚስቶች (ሴቶች) ብቻ 9 (2 ከመቶ) የንብረት ባለቤት መሆናቸውን ገልጸዋል። ምንም እንኳ እንደነዚህ አይነት ሃብቶች በተጋቡ ጥንዶች መካከል የጋራ ንብረቶች መሆናቸው ቢታወቅም በወንዶች እና በሴቶች መካከል በግል የተመዘገቡ ሃብቶች በአንጻራዊነት ልዩነት መኖሩን ጥናቱ ያሳያል።

**የሴቶችን የውሳኔ ሰጭነት ሚና የሚወስኑ ሁኔታዎች፡- መኖሪያ አካባቢ**

**የሚኖሩበት የዞን አስተዳደር**

የጥናቱ ተሳታፊዎች የሚኖሩበት የዞን አስተዳደር ወይም መኖሪያ አካባቢ አንዱ የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት የሚወስን ጉዳይ ነው።  ይህ ጥናት በአንጻራዊነት ከፍ ያለ ቁጥር ያላቸው ሴቶች ከማዕከላዊ ጎንደር ሲሆኑ ምዕራብ ጎጃም እና ደቡብ ጎንደር በቅደምተከተላቸው ይከተላሉ። ዝቅተኛ የሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ብቃት በደቡብ ጎንደር ዞን ታይቷል። በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የሴቶች ውሳኔ ሰጪነት ብቃት በማዕከላዊ ጎንደር 46 ከመቶ ሲሆን በምዕራብ ጎጃም 29 ከመቶ እንዲሁም በደቡብ ጎንደር 26 ከመቶ ነው። በሌላ በኩል ጤናን በተመለከተ የሚደረግ የውሳኔ ሰጪነት ተሳትፎ በደቡብ ጎነደር 28 ከመቶ ሲሆን በማዕከላዊ ጎንደር እና በምዕራብ ጎጃም 37 ከመቶ ነው። በማዕከላዊ ጎንደር የሚኖሩ ሴቶች ደቡብ ጎንደር ዞን ከሚኖሩ ሴቶች ጋር ሲነጻጸር 9 ጊዜ የበለጠ የውሳኔ ሰጪነት ብቃት እንዳላቸው ጥናቱ ያመለክታል።

**ከተማ በሚኖሩ እና ገጠር በሚኖሩ ሴቶች መካከል**

የመኖሪያ አካባቢ የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ከሚወስኑ ጉዳዮች አንዱ ነው። ይህ ጥናት እንደሚያመለክተው 96 ከመቶ የሚሆኑት በከተማ የሚኖሩ የጥናቱ ተሳታፊዎች የውሳኔ ሰጪነት ብቃት አላቸው። በአንጻሩ 86 ከመቶ የሚሆኑት ገጠር የሚኖሩ የጥናቱ ተሳታፊዎች የውሳኔ ሰጪነት ብቃት አላቸው።ይህ ሁኔታ ከተማ ከመኖር ጋር ተያይዞ ከሚገኙ የተሻለ የአገልግሎት፣ የመረጃ፤ የግንዛቤ እና የስራ እድል አቅርቦት ጋር ሊያያዝ ይችላል። በተለያዩ ሌሎች ሃገሮች ላይ የተካሄዱ ጥናቶችም[7,8] በተመሳሳይ ከተማ የሚኖሩ ሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ገጠር ከሚኖሩ የተሻለ እንደሆነ አሳይተዋል።

**የባሎች የትምህርት ደረጃ**

የባሎች የትምህርት ደረጃ ሌላኛው የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት የሚወስን ጉዳይ ነው። በዚህ ጥናት መሰረት ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ የገቡ ባሎች ያሏቸው ሴቶች 97 ከመቶ የውሳኔ ሰጪነት ብቃት አላቸው። ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ባሎች ያሏቸው ሴቶች ያልተማሩ ባሎች ካሏቸው ሴቶች 3 ጊዜ ከፍ ያለ የውሳኔ ሰጪነት ብቃት አላቸው። ከዚህ የምንረዳው ትምህርት በአጠቃላይ የሰዎችን አስተሳሰብ እንደሚያሻሽል ነው። ስለሆነም የተማሩ ባሎች ስለሴቶች እኩልነት የተሻለ ግንዛቤ ሊኖራቸው ስለሚችል የሚስቶቻቸውን ፍላጎት፣ መብትና ነጻነት በቤት ውስጥ ያከብራሉ። ይህ ሁኔታ በሌላ መንገድ የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ያሳድጋል። ይህ ውጤት በሌላ አገር ከተደረገ አንድ የጥናት ዉጤት ጋር ተመሳሳይ ነዉ[9]። በእዚህ ጥናት የጥንዶች የትምህርት ደረጃ የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንዳለው ተጠቁሟል።

**በማህበራዊ ስብስቦች ላይ የመሳተፍ ልምድ**

በማህበራዊ ስብስቦች ላይ የመሳተፍ ልምድ የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ከሚወስኑ ጉዳዮች አንዱ ነው። ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ በማህበራዊ ስብስቦች መሳተፍ ማለት የኢ-መደበኛ የቁጠባ ማህበራት አባል መሆን፣ የሃይማኖታዊ ማህበራት አባል መሆን፣ የእራስ አገዝ ቡድኖች አባል መሆን፣ እና ሌሎች የማህበረሰብ ትስስሮች ላይ መሳተፍን ያካትታል። በዚህ ጥናት ከተሳተፉት ሴቶች ውስጥ 255 (60 ከመቶ) የሚሆኑት ሴቶች ቢያንስ የአንድ ማህበራዊ ስብስብ አባል ናቸው። በእነዚህ የማህበረሰብ ስብስቦች ላይ የሚሳተፉ ሴቶች ከማይሳተፉት ይልቅ 4 ጊዜ የበለጠ የውሳኔ ሰጪነት ብቃት አላቸው። ይህም የሆነው እነኝህ የማህበረሰብ ስብስቦች ሴቶች ሃሳባቸውን በአደባባይ የመግለጽ እድል እንዲዳብር ስለሚያደርጉ እና በእራስ የመተማመን መንፈሳቸውን፣ እውቀታቸውን፣ የመረጃ ልውውጣቸውን እና ግንዛቤያቸውን ስለሚያሳድጉ ነው።

## 4. የጥናቱ መደምደሚያ እና ምክረ ሃሳቦች

ይህ የዳሰሳ ጥናት የተካሄደው በቤተሰበብ ደረጃ የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ለመቃኘት ነው። ለጥናቱ የሚያስፈለጉ መረጃዎች በአማራ ብሄራዊ ክልል ከሚኖሩ 424 በትዳር ላይ ያሉ ሴቶችን በማሳተፍ እና መጠይቅ በማድረግ የተገኘ ነው። የውሳኔ ሰጪነት እና የሃብት ባለቤትነት የሚሉ ሁለት ዋና ዋና መመዘኛዎችን በመጠቀም የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ደረጃ አመላካች መበየን የተቻለ ሲሆን እነኝህ ሁለት መለኪያዎች በየራሳቸው በርካታ ጠቋሚዎችን በመጠቀም የተገኙ ናቸው።

ይህ ጥናት የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ደረጃ እና ወሳኝ ሁኔታዎችን በተመለከተ በጣም ጠቃሚ መረጃዎችን አቅርቧል። በዚህ ጥናት መሰረት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው (91 ከመቶ) ሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ብቃት አላቸው። ይሁን እነጂ በኢኮኖሚያዊ እና ግላዊ ጉዳዮች ዙርያ ያለው የሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ተሳትፎ በሚፈለገው ደረጃ ባለመሆኑ የሴቶችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ለማሻሻል በፖሊሲ የተደገፈ እርምጃ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው።

ይህ ጥናት የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ደረጃ በገጠር እና በከተማ ያለውን ልዩነት አሳይቷል። በገጠር የሚኖሩ ሴቶች በከተማ ከሚኖሩ ሴቶች ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ የውሳኔ ሰጪነት ብቃት እንዳላቸው አሳይቷል። በተጨማሪም የሚኖሩበት የዞን አሰተዳደር፣ የባል የትምህርት ደረጃ፣ እንዲሁም በማህበረሰብ ስብስቦች ላይ የሚደረግ ተሳትፎ የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት የሚወስኑ ሁኔታዎች በመሆን ተለይተዋል። በግልጽ እንደምንገነዘበው ሴቶች

ከወንዶች እኩል አይታዩም ስለሆነም የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ለማሻሻል ብዙ መሰራት ያለባቸው ስራዎች አሉ፡፡

## ምክረ-ሃሳቦች

- በገጠርና በከተማ እንዲሁም በዞናዊ አስተዳደሮች መካከል የሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ደረጃ ልዩነት ስለታየ የብሄራዊ እና ክልላዊ የልማት ፖሊሲዎች ይህን ታሳቢ ያደረጉ እና የገጠር ሴቶችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ላይ ትኩረት መስጠት አለባቸው፡፡
- የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት ማሳደግ ካለወንዶች ተሳትፎ የሚቻል አይደለም፡፡ ስለሆነም ፖሊሲ አውጪዎች ወንዶችን ማስተማር እና በሂደቱ ማሳተፍ አስፈላጊነቱን ተገንዝበው ለተግባራዊነቱ መስራት ያስፈልጋል፡፡
- እንደአጠቃላይ በኢኮኖሚያዊ ውሳኔ ሰጪነት ላይ በተለይ ደግሞ በአንዳንድ የኢኮኖሚያዊ ውሳኔ ሰጪነት አመላካቾች ላይ ውስንነቶች እንዳሉ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ ይህ ደግሞ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ አቅም በማሻሻል ዙሪያ ብዙ መሰራት እንዳለበት አመላካች ከመሆኑም ባሻገር አሁን ያሉትን የተለያዩ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞች መፈተሽ እና ማሻሻል እንደሚገባ ያሳያል፡፡
- የሴቶችን የውሳኔ ሰጪነት ብቃት በተለይም በገንዘብ ነክ ጉዳዮች እና በዋና ዋና ሃብቶች ላይ ያላቸው የውሳኔ ሰጪነት ሚና ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ማህበረሰቡ ስለሴቶች ያለውን የተዛባ አመለካከትና እምነት መቀየርን አላማ ያደረጉ ስልጠናዎች፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች እና ሌሎች ተግባራት ማከናወን አስፈላጊ ነው፡፡

## 5. የተመረጡ ማጣቀሻዎች


1. UNFPA (2008). Gender Inequality and women's Empowerment. In-depth analysis of the Ethiopian demographic and health survey. Addis Ababa: UN and Ethiopian Society of Population Studies.
2. Tefera Assefa (2018). Nature of women empowerment in Ethiopia: constitutional and policy provisions. Dilla: Dilla University (Unpublished report, www.researchgate.net/publication/321753588).
3. UN Women (2014). Preliminary Gender Profile of Ethiopia. Addis Ababa: UN. (https://2012-2017.usaid.gov).
4. Office of Women, Children and Youth Affairs (2022). Overview of Enhancing Women's Leadership and Empowerment Project in Amhara Region. Unpublished Report.
5. CSA (Central Statistical Agency). (2013). Population Projections for Ethiopia 2007-2037. Addis Ababa; CSA.
6. Ngome, Angella N. (2003). Gender Division of Labour and Women's Decision-Making Power in Rural Households: The Case of Mbalangi, Ediki and Mabonji Villages of Meme Division. Buea: University of Buea, Department of Women and Gender Studies (Master's Thesis).

7. Brajesh, Shekhar, C. (2015). Level of women empowerment and it's determinates in selected south Asian countries. Journal of Humanities and Social Science (IOSR-JHSS), 20(4): 94-105 (https://doi.org/10.9790/0837-204594105).
8. Musonera, A. and Heshmati, A. (2017). Measuring women's empowerment in Rwanda. In: A. Heshmati, ed. Studies on Economic Development and Growth in Selected African Countries, pp. 11-39. Singapore: Springer. (https://doi.org/10.1007/978-981-10-4451-9_2)
9. Donta B., Nair S., Begum S., Prakasam C.P. (2016), Association of domestic violence from husband and women empowerment in a slum community, Mumbai Journal of Interpersonal Violence 31(12): 2227–39. (https://doi.org/10.1177/0886260515573574.)